EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ትኩረት የሚሻው አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም

መድኃኒት በአግባቡ ከተወሰደ ተገቢውን የጤና ውጤት በማስገኘት ይቻላል፤ ታማሚው ጤናው ተመልሶለት ወደ ሥራው በመሠማራት አምራች ዜጋ እንዲሆን ይረዳል፡፡ መድኃኒት በትክክል ካልተወሰድ ደግሞ ሕመምን ከማባባስ ባሻገር ተጠቃሚውን እስከ ህልፈተ ሕይወት ሊዳርግ ይችላል፡፡

መድኃኒት ከሕመምተኛው አንፃር በትክክል አልተወሰደም የሚያስብለው አንደኛው ጉዳይ፤ ሕመምተኛው ሐኪሙ ከአዘዘለት መጠን አብዝቶ አልያም አሳንሶ ሲወስድ ነው፡፡ ሕመምተኛው መድኃኒቱን እንደወሰደ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ የተሻለው መስሎትም ይሁን መድኃኒቱ በፈጠረበት የጎንዮሽ ውጤት ተገፋፍቶ አቋርጦት ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ ሕመምተኛው መድኃኒቱን በአግባቡ አልወሰደም ስንል መድኃኒቱን መወሰድ ባለበት መንገድ አለመውሰድ ሊሆን ይችላል። ይህም የሚታኘክ ሆኖ ሳያኝኩ መዋጥ አልያም በአፍ የማይወሰድ መድኃኒትን በአፍ መውሰድና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

ስለሆነም አንድ ሰው መድኃኒቱን በአግባቡ ተጠቀሞ የሚባለው በምርመራ ለተረጋገጠ በሽታው ትክክለኛውን መድኃኒት፣ በትክክለኛው መጠንና በተገቢው ሰዓት ሲወስድ እንዲሁም ከጤና ባለሙያ የሚሰጠውን ምክር ተግባራዊ ሲያደርግ ነው፡፡

ስለዚህ መድኃኒትን ከጤና ባለሙያው ስንወስድ የሚሰጠንን ምክር በሚገባ ማዳመጥና መተግበር ፣ የታዘዘልንን መድኃኒት ስንወስድ የጤና ባለሙያ ሳናማክር አለማቋረጥ፣ መድኃኒቱን እየወሰድን ችግር ካጋጠመን የጤና ባለሙያ ማማከር፣ መድኃኒቱን ከመውሰዳችን በፊት የአገልግሎት ጊዜ/ዘመን (expired date) መመልከት፣ ከዚህ በፊት መድኃኒቱን ስንወስድ ችግር አጋጥሞን ከሆነ ለሐኪም መናገር፣ ለእኛ የታዘዘውን መድኃኒት ለሌላ ሰው አለማጋራት፣ መድኃኒቶችን እየወሰድን የአልኮል መጠጦችን አለመውሰድ፣ ነፍሰጡር ወይም ጡት የምናጠባ ከሆነ መድኃኒቱን ከመውሰዳችን በፊት ሐኪምን ማማከር፣ ሌሎች መድኃኒቶችን እየወሰድን ከሆነ ወይም በቅርብ ጊዜ ወስደን ከሆነ ለጤና ባለሙያ በዝርዝር መናገር ወይም ማሳየት፤ እንዲሁም ያለ ሐኪም ማዘዣ ወረቀት የሚገኙ መድኃኒቶችን ስንገዛ የመድኃኒት ባለሙያን ምክር መጠየቅ የሚሉትን ወሳኝ ጉዳዮች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል። በተጨማሪም መድኃኒቱን ወስደን የተጠበቀውን ውጤት ካላገኘን የጤና ባለሙያን ማማከር ግድ ይለናል።

ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውንም መድኃኒት በምንወስድበት ወቅት የሚከተሉትን ዐበይት ነጥቦች ከጤና ባለሙያ ጠንቅቀን ልንረዳ ይገባል፡፡ የመድኃኒቱን ስም፣ የመድኃኒቱን ጥቅም፣ መድኃኒቱን መቼና እንዴት እንደሚወሰድ (ለምሳሌ በስምንት ሰዓት ልዩነት፣ ከምግብ በፊት ወይስ ከምግብ በኋላ እንደሚወሰድ)፣ በአንድ ጊዜ ምን ያህል መጠን እንደሚወሰድ፣ ለምን ያህል ቀን እንደሚወሰድ፣ መድኃኒቱ እንዴት እንደሚወሰድ (በአፍ፣ በመርፌ፣ በፊንጥጣ፣ ቆዳ ላይ የሚቀባ ወዘተ…)፣ መድኃኒቱ ሲወሰድ ምን ዓይነት ምግቦችና መጠጦች መወሰድ እንደሌለባቸው፣ መድኃኒቱ በትክክል ባይወሰድ ምን ችግር እንደሚያስከትል፣ መድኃኒቱ የት መቀመጥ እንዳለበት፣ መድኃኒቱ ተረስቶ ሳይወሰድ ቢቀር ምን መደረግ እንዳለበት እንዲሁም የመድኃኒቱ የጎንዮሽ ውጤቶች ምን ምን ናቸው? ለምን ያህል ጊዜስ ይቆያሉ? በምን ዓይነት መንገድስ ልቋቋማቸው እችላለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው።

መድኃኒት በአግባቡ ካልተወሰደ በርካታ ችግሮችን እንደሚያስከትል የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የሕክምናው ጥራት በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፣ መድኃኒቶች ያለአግባብ እንዲባክኑ ያደርጋል፣ አግባብ ላልሆነ ወጪ ይዳርጋል፣ በመድኃኒቱ የሚከሰቱ ተጓዳኝ ችግሮች ወይም ጎጂ ባህሪያት አደጋ ይጨምራል፣ መድኃኒቱ ከበሽታው ጋር የመላመድ ባህሪ እንዲፈጥርና ፍቱንነቱ እንዲቀንስ ያደርጋል። በተጨማሪም ዳግም በዚህ በሽታ ብንያዝ የመዳን እድላችን ይቀንሳል።

ስለሆነም አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም እንዲኖር ከሚያስችሉ ሁኔታዎች መካከል መድኃኒቶችን ከየት መግዛት እንዳለብን ማወቅ ተጠቃሽ ሲሆን ሕጋዊ ከሆኑ የመድኃኒት ማደያ ተቋማት ማለትም ከሆስፒታሎች፣ ከጤና ጣቢያዎች እንዲሁም ከመድኃኒት ቤቶች መውሰዳችንን መዘንጋት የለብንም፡፡

በተለይ መድኃኒቶችን ስናስቀምጥ የሚከተሉትን ጉዳዮች ተግባራዊ ማድረጋችንን ሁሌም ቢሆን ልናስታውስ ይገባል፡፡ ሕፃናት ከማይደርሱበት ቦታ ማስቀመጥ፣ የተለያዩ መድኃኒቶችን በአንድ ዕቃ ውስጥ አቀላቅሎ አለማስቀመጥ፣ ሙቀትና ቀጥታ የፀሐይ ብርሃን ከማይደርስበት ቦታ ማስቀመጥ፣ መታጠቢያ ክፍል፣ በማዕድ ቤት እንዲሁም እርጥበት ባለበት ቦታ አለማስቀመጥ ፣ በመድኃኒቱ ማሸጊያ ላይ ካልተገለጸ ወይም ከጤና ባለሙያ የተለየ ትዕዛዝ ካልተነገረ በስተቀር መድኃኒቱን በጣም ቀዝቃዛ ወይም ሞቃት በሆነ ቦታ አለማስቀመጥ፣ ፍሪጅ ውስጥ የሚቀመጥ መድኃኒት ከሆነ በረዶ መሥሪያ ውስጥ ወይም (freezer) ውስጥ አለማስቀመጥ፣ በልብስ ኪስ ወይም መኪና ውስጥ መድኃኒቱን ለብዙ ሰዓት አለማስቀመጥ ወይም አለማቆየት የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

የፀሐይ ብርሃን፣ ሙቀትና እርጥበት መድኃኒቶችን ለብልሽት ይዳርጋሉ፡፡ ስለሆነም መድኃኒቶችን በቤት ውስጥም ሆነ በማንኛውም ስፍራ ስናስቀምጥ ከእነዚህ ነገሮች መጠበቅ ካልቻልን የተበላሹ መድኃኒቶችን በመውሰድ ለከፋ የጤና ችግሮች ልንዳረግ እንችላለን፡፡ በተጨማሪም መድኃኒትን በቤት ውስጥ ስናስቀምጥ ሕፃናት በቀላሉ አግኝተዋቸው ጉዳት ላይ እንዳይወድቁ በጥንቃቄ ልናስቀምጥ እንደሚገባ መርሳት አያስፈልግም፡፡

በጥንቃቄ የማይቀመጥ መድኃኒት በቀላሉ ሊባላሽ ይችላል፡፡ በመሆኑም የተበላሹትን መድኃኒቶች ከደህናዎቹ አይተን በቀላሉ መለየት ስለማንችል ተጠቅመናቸው ለጉዳት ልንጋለጥ እንችላለን። ስለሆነም መድኃኒቶች በአግባቡ ካልተቀመጡ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊትም ሊበላሹ የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይገባናል፡፡ በማንኛውም መንገድ የተበላሸ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈን መድኃኒት ፈጽሞ መጠቀም የለብንም።

በአንፃሩ አገልግሎት ላይ የማይውሉ መድኃኒቶችን ቀድሞ በተዘጋጁበት ማሸጊያ ውስጥ በመክተትና በመሰባበር እንዲሁም ከቆሻሻዎች ጋር በመቀላቀል በአግባቡ ማስወገድ ይገባል። ምክንያቱም በአግባቡ ያልተወገዱ መድኃኒቶች በሰዎችና በእንስሳት ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉና።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ